Bundesamt
für Migration
und Flüchtlinge

**የጀርመንኛ ቋንቋና አኗኗር ትምህርትን የሚመለከት መረጃ መስጫ ወረቀት**

ለውጭ ዜጎች፣ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በጀርመን ሃገር ለኖሩ የአውሮጳ ኅብረት ዜጎችና በቂ የጀርመን ቋንቋ ችሎታ ለሌላቸው የጀርመን ዜግነት ላላቸው በሙሉ።

የተከበራችሁ የዚህች ሃገር ዜጎች፣

እርስዎ ከረጅም ጊዜ ጀምረው በጀርመን የኖሩ የውጭ ዜጋ እና/ወይም የአውሮጳ ኅብረት ዜጋ ከሆኑ ወይም በቂ የጀርመንኛ ቋንቋ ዕውቀት ከሌልዎት፣ የጀርመንኛ ቋንቋና አኗኗር ትምህርትን ለመማር እንዲፈቀድልዎት በስደተኞችና ሰፋሪዎች ፌደራል ቢሮ (Federal Office for Migration and Refugees) ዘንድ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ።

በትምህርት ገበታ ላይ ያሉ ሕፃናት ልጆች፣ ታዳጊ ወጣቶችና ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች የጀርመንኛ ቋንቋና አኗኗር ትምህርትን መማር አያስፈልጋቸውም።

<u>የጀርመንኛ ቋንቋና አኗኗር ትምህርት ምንድነው?</u>

የእኛ ጠቅላይ የጀርመንኛ ቋንቋና አኗኗር ትምህርት የ 600 ሰዓታት የቋንቋ ትምህርትን እና የ 100 ሰዓታት የአኗኗር ገለጻ ትምህርትን ያካትታል። የቋንቋ ትምህርት ኮርሱ እያንዳንዳቸው 100 ሰዓታት በውስጣቸው የያዙ ክፍሎችን ይዟል። የመጀመሪያዎቹ 300 ሰዓታት መሰረታዊ የቋንቋ ስልጠና ኮርስን የተመለከቱ ሲሆን፣ ቀጣዮቹ 300 ሰዓታት ደግሞ የመካከለኛ ደረጃ የቋንቋ ችሎታ ስልጠና ትምህርት ክፍሎችን የተመለከቱ ናቸው።

በቋንቋው ትምህርት ወቅት፣ ለዕለት ተዕለት ኑሮ በንግግር እና በጽሑፍ ለመግባቢያነት የሚያስፈልግዎትን ቃላቶችን ይማራሉ። ከነዚህም መሃል ጉዳይዎትን ከሚመለከቱ ባለሥልጣናት ጋር መነጋገር፣ ከጎረቤትዎና ከሥራ ባልደረቦችዎ ጋር መወያየትና ደብዳቤዎችን መጻፍ እና ቅጾችን መሙላት የመሳሰሉ ይገኙበታል።

በአኗኗር ገለጻው ትምህርት ወቅት ደግሞ ስለ ጀርመን አገር አኗኗር ሕግና ሥርዓት እንዲሁም ባህል እና የቅርብ ጊዜ ታሪክ ግንዛቤ እንዲኖርዎት ይደረጋል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ሴቶችን፣ ወላጆችን፣ ታዳጊ ወጣቶችን እና እንዲሁም የማንበብ እና የመጻፍ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ብቻ የተለመከቱ ልዩ የጀርመንኛ ቋንቋ እና አኗኗር ኮርሶችም አሉ። እነዚህ ኮርሶችን ተምሮ ለመጨረስ እያንዳንዳቸው 1.000 ሰዓታትን ይወስዳሉ። በፍጥነት መማር ምርጫዎ ከሆነ፣ 430 የስልጠና ሰዓታትን በሚወስደው ልዩ የተጠናከረ ኮርስን መውሰድ ይችላሉ።

እያንዳንዱ ኮርስ ከመጀመሩ በፊት፣ ኮርሱን የሚሰጠው ክፍል የእርስዎን የቋንቋ ብቃት ደረጃ ለመወሰን እና ለእርስዎ ተገቢነት ያለው ኮርስ ላይ መመደብ እንዲችሉ የመግቢያ ፈተና እንዲወስዱ ያደርግዎታል።

KNr. 630.009j Amharisch BAMF 12/2016

የመጨረሻውን ፈተና መፈተን

የመጨረሻው ፈተና የቋንቋ ብቃት መመዘኛ ፈተና እና የአኗኗር ገለጻ ኮርስ ፈተናን ያካተተ ይሆናል። በቋንቋ ብቃት መመዘኛ ፈተናው ላይ በቂ የጀርመንኛ ቋንቋ ችሎታ እንዳልዎት ካሳዩ እና የአኗኗር ገለጻ ኮርስ ፈተናውን ካለፉ፣ የጀርመንኛ ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርትን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀዋል ማለት ሲሆን ለዚህም

"የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት ምስክር ወረቀት" ("Integration Course Certificate") ይሰጥዎታል።

ፈተናውን ሳያልፉ ቢቀሩ፣ ያገኙትን ውጤት የሚያንጸባርቅ ምስክር ወረቀት ብቻ ይሰጥዎታል።

የመጨረሻው ፈተና የሚሰጠው ከክፍያ ነጻ ነው።

በጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት በመማር የሚገኙ ጥቅማጥቅሞች

ከአውሮጳ ኅብረት ውጭ ከሆኑ ሃገራት የመጡ የውጭ ዜጎች ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ በጀርመን ሃገር ውስጥ ለማግኘት የተወሰኑ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። ከነዚህ በርካታ መስፈርቶች መካከል አንዱ በቂ የሆነ የጀርመንኛ ቋንቋ ችሎታ እንዳለ ማስመስከር እና በጀርመን ስላለው ሕጋዊ፣ ማኅበራዊ እና ምጣኔ ሃብታዊ ሁኔታ መሰረታዊ ዕውቀት እንዳለ ማረጋገጥ ይገኙባቸዋል። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ የሚችሉት የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርትን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ሲቻል ነው። ይህ ሆኖ ከተገኘ፣ ከተገቢው ጊዜ ቀደም ብሎ የዜግነት መብትም ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

በተጨማሪ፣ በጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት ወቅት የሚቀስሙት የጀርመንኛ ቋንቋ ክህሎቶች በጀርመን ሃገር የሚኖርዎትን ኑሮ ቀላል ከማድረጉ ባሻገር ሥራ የማግኘት ዕድልዎን የሰፋ እንዲሆን ያደርጋል።

የጀርመን ቋንቋና አኗኗር ትምህርትን ለመውሰድ ከፌደራል ቢሮ ፈቃድ ስለማግኘትና በትምህርት ሰጪ ተቋማት ስለመመዝገብ

---

የምዝገባ ማመልከቻውን በተሟላ እና ሊነበብ በሚችል መልኩ እባክዎ ይሙሉት። የምዝገባ ማመልከቻዎን በመሙላት ላይ እንዲያግዝዎት በአቅራቢያዎ ያለ ትምህርት ሰጪ ተቋምን ማነጋገር ይችላሉ። ይህን ካደረጉ በኋላ፣ የተሞላውን የምዝገባ ማመልከቻ ለፌደራል ቢሮው የአካባቢዎ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ይላኩት።

የጀርመን ቋንቋና አኗኗር ትምህርትን እንዲማሩ ፈቃድ ሲሰጥዎት፣ ከፌደራሉ ቢሮ በጽሑፍ የሚሰጥ ማረጋገጫ ሰነድ (ፈቃድ መስጫ ወረቀት) ይደርስዎታል። በዚሁ ጊዜ ላይም፣ ከሚኖሩበት ቦታ አቅራቢያ ያሉ የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት ሰጪ ተቋማትን ዝርዝር የያዘ ሰነድ ይደርስዎታል።

የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት እንዲማሩ የሚሰጥዎት ፈቃድ ለአንድ ዓመት ያገለግላል። የሚደርስዎት የማረጋገጫ ሰነድ "ፈቃዱ እስከ ... ድረስ ያገለግላል" የሚል የጊዜ ገደብ የሚኖረው ሲሆን በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ በየጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት ሰጪ ተቋም ተመዝገበው ትምህርትዎን መጀመር አለብዎት። በመሆኑም፣ ለየጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት ሰጪ ተቋሙ የፈቃድ መስጫ ወረቀትዎን በማቅረብ እባክዎ በተቻልዎት ፍጥነት ቶሎ ይመዝገቡ!

የትምህርት መስጫ ተቋሙ መቼ ትምህርቱን መጀመር እንዳለብዎት እርስዎ ምዝገባዎን ባጠናቀቁ በ3 ሳምንታት ውስጥ ለእርስዎ የማሳወቅ ግዴታ አለበት። በዚህ ጊዜ ውስጥ ምንም የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት ከሌለ፣ ትምህርት መስጫ ተቋሙ ይህንኑ ለእርስዎ ማሳወቅ አለበት። ትምህርቱ እስኪጀመር መጠበቅ ወይም በሌላ የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት መስጫ ተቋም ውስጥ የመመዝገብ ምርጫው የእርስዎ ነው። በሌላ ትምህርት መስጫ ተቋም ለመመዝገብ ከመረጡ፣ ቀደም ሲል ተመዝግበውበት የነበረው ትምህርት መስጫ ተቋም የተሰጥዎትን ፈቃድ መስጫ ወረቀት ለእርስዎ መመለስ አለበት።

ተገቢ የሆነ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት

የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት የታሰበለትን ዓላማ መምታት እንዲችል፣ የተወሰኑ ደንቦች መከበር አለባቸው።

ይህ በመደበኛነት በትምህርት ገበታ ላይ ሳያቋርጡ መገኘት እና የመጨረሻውን ፈተና መውሰድ ያካትታሉ። በመደበኛነት በትምህርት ገበታ ላይ ሳያቋርጡ መገኘት ለመጓጓዣ የወጣ ገንዘብን ለማስመለስ ወይም በሌላ ጊዜ ትምህርቱን መማር ለመቀጠል በተጨማሪ አስፈላጊ ነው። ከፈልጉ በመደበኛነት በትምህርት ገበታዎ ላይ ሳያቋርጡ ስለመገኘትዎ ማረጋገጫ በጽሑፍ ሊሰጥዎት ይችላል።

ከአንድ ትምህርት ሰጪ ተቋም ወደ ሌላ ትምህርት ሰጪ ተቋም መቀየር የሚቻለው አንድ የተጀመረ የኮርሱ ክፍል ሲጠናቀቅ ብቻ ነው። የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት ወጪ

---

ለትምህርት ሰጪ ተቋሙ በእያንዳንዱ ትምህርት ክፍለ ጊዜ 1.95 ዩሮ (EUR 1.95) መክፈል አለብዎት። ይህ ክፍያ እያንዳንዱ ባለ 100 ትምህርት ክፍለ ጊዜ ኮርስ

ከመጀመሩ እና የአኗኗር ገለጻ ትምህርቱ መሰጠት ከመጀመሩ በፊት መከፈል አለበት። በመማሪያ ክፍልዎ ሳይገኙ ቢቀሩ፣ ሳይማሩ ላመለጥዎት ትምህርት የከፈሉት ገንዘብ ተመላሽ አይደረግልዎትም። ምንም ዓይነት ገቢ ከሌልዎት፣ የእርስዎን የመኖሪያ ወጪዎች እንዲሸፍን ግዴታ የተጣለበት ግለሰብ ክፍያዎን ሊከፍልልዎት ይገባል።

መሰረታዊ የቀለብ ድጋፍ (Arbeitslosengeld II)፣ የሥራ አጥነት ክፍያ ወይም የማኅበራዊ ዋስትና ክፍያ (Sozialhilfe) የሚቀበሉ ከሆነ ወይም ባልዎት ዝቅተኛ ገቢ ምክንያት ክፍያ መፈጸሙ ለእርስዎ አስቸጋሪ ከሆነ ክፍያ ከመክፈል ነጻ እንዲሆኑ ሊደረጉ ይችሉ ይሆናል። ከክፍያ ነጻ ለመደረግ፣ በሚኖሩበት አካባቢ ላለው የፌዴራሉ ቢሮ የክልል ተወካይ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት (የአድራሻ ዝርዝሩን ይመልከቱ) በጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ አለብዎት።

የገንዘብ ችግር እንዳለብዎት የሚያስረዳ ማስረጃ እባክዎ ዓባሪ ያያዙ (ተዛማጅነት ያለው ምስክር ወረቀት ቅጂ፣ ለምሳሌ የሥራ አጥነት ክፍያ ማስታወቂያ፣ የማኅበራዊ ዋስትና ክፍያ ማስታወቂያ፣ የመኖሪያ ቤት ድጎማ ማስታወቂያ፣ የተማሪ የገንዘብ ድጋፍ (BAFöG)፣ በልጅ ለቤተሰብ የሚሰጥ የገቢ ተጨማሪ ድጋፍ (Kindergeldzuschlag)፣ በጥገኝነት ጠያቂዎች ጥቅማጥቅሞች ሕግ (Asylum Seekers Benefits Act) የሚሰጥ ክፍያ፣ ከልጆች ማቆያ ቦታ ክፍያ ነጻ ስለመሆን የተሰጠ ማረጋገጫ (Kita-Gebühren)፣ የዜና ማሰራጫ ፈቃድ ክፍያ ነጻ ስለመሆን የተሰጠ ማረጋገጫ (GEZ-Gebühren)፣ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎቶች ቅናሽ ክፍያ (Sozialticket)፣ በ SGB VIII መሰረት የተሰጠ የልጅ እና የወጣቶች ማኅበራዊ ዋስትና አገልግሎቶች መስጫ ወዘተ)። የሚቻል ከሆነ፣ ማመልከቻዎን ኮርሱ ከመጀመሩ በፊት ያስገቡ።

ተመላሽ ገንዘብ

ከኦገስት12፣ 2007 በኋላ የመጨረሻውን ፈተናዎን ካለፉ፣ ከከፈሉት ክፍያ 50 በመቶ ያክሉን የፌደራሉ ቢሮ ገንዘብዎን ተመላሽ ያደርግልዎታል። ይህ ተፈጻሚነት የሚኖረው ኮርሱን እንዲወስዱ ፈቃድ በተሰጠበት እና በመጨረሻው ፈተና መካከል ያለው የጊዜ ልዩነት ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ከሆነ ብቻ ነው። ተመላሽ ገንዘብ ለመቀበል፣ ተገቢነት ወዳለው የፌደራሉ ቢሮ በአካባቢዎ የሚገኝ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርብዎታል።

## የመጓጓዣ ወጪዎች

ከክፍያ ነጻ እንዲሆኑ በፌደራሉ ቢሮ ከተወሰነልዎት፣ ኮርሱ የሚሰጥበት ቦታ ከቤትዎ ከ3 ማይል ርቀት በላይ በሚገኝ ቦታ ላይ ከሆነ ለሚያወጡት የመጓጓዣ ወጪ ድጎማ ይሰጥዎታል። እንደ ደንብ፣ የሚሰጥዎት ድጎማ ወደ አቅራቢያዎ የሚገኝ ትምህርት ሰጪ ተቋም ለሚያደርጉት ደርሶ መልስ ጉዞ ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት። የመጓጓዣ ወጪ ድጎማ ለማግኘት ወደ ፌደራሉ ቢሮ የአካባቢዎ ቅርንጫፍ ቢሮ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርብዎት እንደሆነ ለማረጋገጥ እባክዎ ከትምህርት ሰጪ ተቋምዎ ጋር ይነጋገሩበት። እንደ ደንብ ሆኖ፣ የመጓጓዣ ወጪ ድጎማ የሚሰጠው ትምህርትን ሳያቋርጡ በቀጣይነት መማር ሲቻል ብቻነው።

## የመካከለኛ ደረጃ የቋንቋ ትምህርት ኮርስን ዳግመኛ መውሰድ

በፈተናው ወቅት በቂ የጀርመንኛ ቋንቋ ችሎታ እንዳልዎት ለማሳየት ሳይችሉ ቢቀሩ፣ ከኮርሱ እስከ 300 ሰዓታት ያክል በድጋሚ ትምህርት መማር እና ከክፍያ ነጻ በድጋሚ የቋንቋ ፈተናውን መፈተን ይችላሉ። በመደበኛነት ከትምህርት ገበታ ሳይቀሩ ትምህርትን መከታተል ቅድመ ሁኔታ ነው።

የመሰረተ ትምህርት (ማንበብ እና መጻፍ) በሚማሩበት ጊዜ የቋንቋ ብቃት ፈተናውን መውሰድ አያስፈልግም።

ትምህርትን በድጋሚ ለመማር፣ ተገቢነት ወዳለው የፌደራሉ ቢሮ በአካባቢዎ የሚገኝ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርብዎታል።

## ሌላ ምን ማወቅ ይኖርብዎታል፥

በዚህ መረጃ መስጫ ወረቀት ላይ የተጠቀሱ ሁሉንም ማመልከቻዎች በእርስዎ ትምህርት መስጫ ተቋም በኩል በእርስዎ የውጭ ዜጎች ምዝገባ ቢሮ ወይም በእርስዎ የአካባቢ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በኩል ማግኘት ይችላል። በተጨምሪ፣ ቅጾቹን በእኛ የድር ጣቢያ www.bamf.de ላይ ማግኘት ይችላል። የመረጃ መስጫ ወረቀቱ የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርትን ለመከታተል አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ መረጃ ይዟል። ዝርዝር መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ትምህርት ሰጪውን ተቋም ያነጋግሩ።

እኛ ከምንሰጣቸው አገልግሎቶች በተጨማሪ፣ እባክዎ የስደተኞች ምክር አገልግሎት ማዕከላትን እና የወጣት ስደተኞች አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለመጠቀምም ከግምት ያስገቡዋቸው። እነርሱ ጥያቄ አቀራረብ ላይ ሊያግዙዎት፣ ለጥያቄዎችዎ መልስ ሊሰጥዎት፣ ችግርዎን ሊቀርፉልዎት እና ለእርስዎ ተገቢነት ያለውን የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት እንዲያገኙ ሊያግዝዎት ይችላሉ። የስደተኛ መረጃ መስጫ ማዕከላት እና የወጣት ስደተኞች አገልግሎት መስጫ ተቋማት እርስዎ በሚኖሩበት አካባቢ የሚገኙባቸው ቦታዎች ከፌደራሉ ቢሮ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የእርስዎን የስደተኛነት ጉዳይ ከሚከታተለው ባለሥልጣን ዘንድ ወይም በሚከተለው አድራሻ በመስመር ላይ (ኦንላይን) ማግኘት ይችላል፥

www.bamf.de

የጀርመን ቋንቋ እና አኗኗር ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ በድንገተኛ አደጋ ኢንሹራንስ የመድህን ሽፋን እንደሌልዎት እባክዎ ልብ ይበሉ።